# ስለ "ኦሮሚያ" የፈጠራ ክልልና ቁቢ (የላቲን ፊደል)

## ክፍል ፪

## ማነው የማንን አገር የወረረው?

በማንስ አገር የማን "ኦሮሚያ ሪፑብሊክ" ይመሠረታል? የጋላ ጎሣስ ድርጅቶች ይልቁንም ኦነግ "ኦሮሚያ" የሚለውን የቅዠት ትርክቱን አገር ለመፍጠር የሚያቀርበው መከራከሪያ ነጥብ በዘመነ ዳግማዊ አጤ ምኒሊክ "የአበሻ ንጉሥ ነገሥት የቅኝ ተገዥ ሆነናል" ነው። ዳሩ ግን ከዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በፊት ከ16ኛው ሁለተኛ አጋማሽ ከግራኝ አሕመድ ያሥራ አራት ዓመታት ወረራ ማግስት ከዛሬይቱ ኬኒያና ሱማሌ ጠረፍ ቦረና ባንዴራ ጁባ ወንዝ ሸለቆ ፈልሶ በሉባ ወራሪ ጦር በጥንታዊት ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሁለቱ ጋላ ነገዶች መጤ ሰፋሪዎች ተንሰራፍቶ መስፈር ለኦነግና ብጤዎቹ "ቅኝ አገዛዝ" አይባልም። የጋላ ልዩ ልዩ ጎዎች በሉባ ወራሪ የደፈጣ ውጊያ ስልት ለ200 ዓመት (1537-1755) ሳያቋርጥ ተመላልሰው፤ ከአረብና የቱርካ ቅጥረኛ ከግራኝ አህመድ ጅሃዳዊ እልቂትና ፍጅት እጅግ በጣም ተራቁቶና ተዳክሞ በነበረበት ወቅት ነው ዘላን ጋሎች ይህን አመቺ ሁኔታ ተጠቅመው ያላቋረጠ ወረራና ዝርፊያ የጀመሩት። ከግራኝ አሕመድ ወረራ የተረፉትን ነው ዘላን ጋሌች በየደረሱበት የጨረሷቸው። በጋላ ወረራ የተፈጸመው የኢትዮጵያውያን የሕይወት ዕልቂት፣ የንብረት ውድመት ሕፃን፣ ሽማግሌ፣ አሮጊት በማይለይ ፍጹም አረመኔያዊ የደፈጣ ውጊያ ስልት ኢትዮጵያውያን ጉራጌዎች፤ ዐማሮች፣ አርጎባዎች ሃድያዎች፣ ትግሬዎች፣ ጎንጋዎች፣ የሞች፣ ጋሞዎች፣ ሲዳማዎች ወዘተረፈ በሽብርና ዑዑታ ያሳለፉትን ረጅም እጅግ መራራ የመከራ ዘመናት እንርሳው ብለን የወደፊቱን በማየት፣ በተስፋፌ ወራሪነት የጋላ ዘላን ጎሣዎች መጥተው በምድራችን ከሠፈሩ በኋላ ከእልቂቱ በአምባዎችና ገደልማ ሸለቆዎች ላይ ሰፍሮ ከተረፈው ነባር ሕዝብ ጋራ አብሮ በመኖር የባሕልና ቋንቋ መወራረስ በማድረግ፣ ይልቁንም የወረሞ ጋላ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን አዲስቷን ኢትዮጵያ በአንድነት አብረው የገነቡበትን ማኅበረሰባዊ መስተጋብር፣ ለኢትዮጵያ ሕልውና ነፃነት ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈሉ መሆናቸውን ተገንዝበን ያለፈውን የጋላ ጎሣ በጣም አስከፊ የወረራና ዝርፊያ ታሪክ እስከዛሬ በመጽሐፍ በሰፊው ሳይሠፍር፣ በሥርዓተ ትምህርት የጎላ ምዕራፍ ሳይሰጠው ቆይቷል። ይህም ስለሆነ ነው ከዘመነ ወታደራዊ ደርግ ሥልጣን መያዝ ጀምሮ እራሳቸውን "ኦሮሞ" ብለው በአዋጅ ማስጠራትና መጠራት የጀመሩት። የጋላ ልሂቃን በጠባብ ጎሰኝነት ስሜት ተለክፈው እንደ ኦነግ ያሉት የኦሮሞ ታሪክ እየተባለ ፍጹም የፈጠራ ወሬ ተዘጋጅቶ ፀረ ኢትዮጵያ፤ ፀረ ዐማራ ትርክት በሰፊው ሲነዛ ቆይቷል፤ ዛሬም ይነዛል። የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የረጅም ዘመን ታሪክ የጎሣ ነፃ አውጪ ነፍሰ ገዳዮች፣ የቅጥረኛ ፖለቲከኞችና ምሁር ተብየዎች አገር በቀልና ባሕር ማዶ የዘርኝነት አቀንቃኞች እንደፈለጉትና እንደሚመኙት ዐይናቸውን በጨው አጥበው እየዋሹና በምናባቸው እየፈጠሩ የሚፎልሉበት ሰፊ መስክ ሆኗል። በየቀኑ፣ በየሳምንቱ፣ በየወራቱ በየጋዜጣውና መጽሔቱ፣ እንዲሁም በመጸሐፍ መልክ የሚሰፍረው "የኦሮሞ ታሪክ፣ የኦሮሞ ባሕል፣ የኦሮሞ ቋንቋ፣ የኦሮሞ ሃይማኖት" ወዘተረፈ. ስፍር ቁጥር የለውም። ይህም በአብዛኛው የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ ማንቋሸሺያ፣ የነገሥታቱ (በተለይም የዳግማዊ አጤ ምኒልክ) መሳደቢያ ቅራቅንቦ ነው። በኢትዮጵያ ወራሪውና መጤ ሰፋሪው ዘላን ጋላ ሆኖ ሳለ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪውን ሕዝበ ክርስቲያን ለይተው "የአበሻ ወራሪ፣ ነፍጠኛ፣ ጨቋኝ፣ ተስፋፊ፣ ቅኝ ገዥ፣ ፊውዳል" እያሉ እነ ኦነግ በሬው ላም ወለድ ውሸት የመንዛት አባዜ ተጠናውቷቸዋል። የኦሮሞ ግንባር ተብየው ጋሎች በወረራ የሰፈሩበትን አካባቢ "ከቅኝ ገዥዋ" ኢትዮጵያ እንደ ሌሎቹ የአፍሪቃ ቅኝተገዥ የነበሩ ሀገራት የራስን እድል በራስ መወሰን መርህ አስገንጥሎ ነፃ "ኦሮሚያን" እፈጥራለሁ ብሎ ይቃዣል። ስለሆነም ነው "ኦሮሞ" ያልሆኑ በብዙ ሚሊዎን የሚቆጠሩ ነዋሪዎችን ከ"ኦሮሚያ ክልል" እንዲወጡ በማለት በሰፊው ሲለፈፍ የቆየውና ያለው።

የቀዝቃዛው ጦርነት አክትሞ የደርግ ወታደራዊ ኮሚኒስት መንግሥት ወድቆ በነወያኔ ሻዕቢያና ኦነግ መሪነት፤ በምዕራባውያን በተለይም በአንግሊዝና አሜሪካ መንግሥታት ርዳታና ድጋፍ የባንቱስታን የጎሣ መንግሥት በአዲስ አበባ ከተመሠረተ በኋላ አጋጣሚውን ተጠቅሞው ኦነግና ትሕነግ ተባብረው ዐማራውን ሕዝብ በዘር ለይተው በያለበት ከፍተኛ ወንጀል ፈጽመውበታል። ኦነግና ትሕነግ ያማራ ተወላጆችን ለይተው በሐረርጌ (በደኖ፣ ወተር፣ አሰቦት) በአሩሲ አርባጉጉ፣ በባሌ፣ በወለጋ፣ በኢሉባቦር አስጨፍጭፈዋል። ዐማሮች ቤት ተዘግቶባቸው በእሳት ጋይተዋል፤ አዘቅት ገደል ተጥለዋል። ከትውልድ ቀያቸው ሃብት ንብረታቸውን ተዘርፈው ተፈናቅለዋል። የኦነግ ተወካዮች ሃላፊነቱን አምነው ከሰነበቱ በኋላ የሚያስከትልባቸውን ችግር ስለተረዱት እነ የሐንስ ለታ (ሌንጮ) ለማስተባበል ላይ ታች ብለዋል። ዳሩ ግን ይህ ድርጊት አስቀድሞ የተዘጋጀ የኦነግ ዓላማ መሆኑን የሚከተለው ማስረጃ በጀርመንኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን ያገናዝቧል።

በ"ኦሮሚያ ክልል" ውስጥ ጋላ ያልሆኑ "መጤ" የውጪ ሰዎች፣

<< አንደኛ ኢትዮጵያውያን (ወረ ይቶጵያ) ማለትም ዐማሮች ቅኝ ገዥ ሰፋሪዎች (ናፍጣዩታ) ወደ መጡበት ይባረራሉ።

ሁለተኛ ፈላሲዎች ሱማሌዎች፣ ጉራጌዎች ወላሞች፣ ሲዳማዎችና ሃድያዎች
ሦስተኛ ከሩቅ አገር የመጡ (ወረ ቢያ ፋጎዳ) እነዚህም አረቦች፣ ግሪኮች፣ አርመኖችና ሌሎች ፈረንጆች በኦሮሚያ መኖርና የኦሮሚያን ሕገ መንግሥት (ሄራ) ከተቀበሉ ብቻ ባሕላቸውንና ቋንቋቸውን፣ ሃይማኖታቸውን ለልጆቻቸው ማስተማር ይችላሉ። >>
(Thomas Zettelmann: Nation der Oromo: (Berlin) 1990, P. 61-62)

ከዚህም ሌላ የኦነግ በሱዳን ተወካይ የነበረው ዶክተር ታድስ ኢባ ከጀርመናዊው ሄልሙት ፋልከንስቶርፈር ጋራ ያደረገውን ቃለ መጠይቅ ያስታውሷል።
ኦነግ ምንድን ነው የሚፈልገው? ኦነግ የሚፈልገው የራስን እድል በራስ መወሰን ፍጹም ነፃነትን ነው። በጀመሪያ ኦሮሚያ ከዋና ከተማዋ ፊንፊኔ ጋራ መመሥርት አለባት። አዎ! መንግሥቱም ኃይለ ማርያምም ሰፋሪ ነው። አዲስ አበባ ፊንፊኔ የኦሮሞ ምድር ናት። በዚያ ያለው ዐማራ ሁሉ ሰፋሪ ነው፣ ቅኝገዥ ነው። ስለዚህ ዐማሮች ከፊንፊኔ ይባረራሉ። መተላለፊያ መንገድ ተዘጋጅቶላቸው ወደ መጡበት ወደ ሰሜን መሄድ ይችላሉ። (Helmut Falkenstoerfer: Aethiopien, Tragic und Chancen einer Revolution, 1986, P62)

ዐማሮችን በሐረርጌ ክፍለ ሀገር (በበደኖ፤ በአሰቦትና በወተር) አስጨፍጭፎ ከወያኔ ትግሬ-ሻዕቢያ ፊት ሲነሳው ፈርጥጦ አሜሪካ የገባው የወያኔ ኢሕአዴግ "ኦሮሚያ ክልል" ቅምጥ ገዥ ሆኖ ሲደነፋ የነበረው ቆቱው የሐረር ጋላ ሐሰን ዓሊ ኢብራሂም "በጭያማችን ሥር ወድቆ እንርገጠው" እንዳለው፣ የኢትዮጵያን ታሪክ ከጀርመን ናዚ ታሪክ ጋር ያመሳሰለበትና "ዲናዝይፊኬሽን" ያስፈልገዋል የተባለበት፤ የነገደ ጋላ በኢትዮጵያ ደጋማ ምድር ጥንት ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ ይኖር የነበረ ጥንታዊ ሕዝብ እንደሆነና ከኢትዮጵያ ውጭ "መጤው" ዐማርኛ፣ ትግሪኛ፣ ጉራጊኛ፣ አርጎብኛ፣ ዛይኛ ወዘተ ተናጋሪው የ"አቢሲኒያ" ወገን ነው እየተብለ የውሸት ትርክት ተነዝቷል፡ "ከክልላችን ይውጣ" ፕሮፓጋንደ ይናፈሳል።

ሌላው የፈጠራ ወሬ ደግሞ "ኦሮሞው 40% ከመቶ እጅ ነው፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የዐማራ ብቻ ነበር" እየተባለ ለአያሌ ዓመታት የሚናፈስው ነጭ ውሸት የከፋፋዩችና ዘረኞች ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎችና አገር በቀል ቅጥረኞቻቸው የእነ ሻዕቢያ፣ ወያኔና ኦነግ የመሳሰሉት የሚያራግቡት ለሥልጣን በአቋረጭ ማግኛው ስልት ነው።
የአማራውን ሕዝብ ቁጥር አሳንሶ፤ የጋላውን ሲበዛ አጋኖ መለፈፍ በቅድሚያ የፕሮቴስታንት ሚሲዎናውናን ልብ-ወለድ ፖለቲካዊ ስሌት ሲሆን ይህም በአፍሪቃ አያሌ ነፍሳትን ለፕሮቴስታንት ክርስትናነት ምልመላ ያስገኝልናል ከሚል ግምትና ምኞት የፈለቀው የነ ዩሐን ክራፍ ስሌት ነው።
በኢትዮጵያ ውስጥ ያማራውን ሕዝብ በዋና ጠላትነት የፈረጁ ወገኖች ሁሉ ባደረባቸው ከፍተኛ ፍርኅትና ስጋት ሳቢያ ዘወትር ብዛቱን ቀንሶ መለፈፍ ዋና ስልታቸው አድርገውታል።

ለምሳሌ ናዚው ሮማን ፕሮቻዝካ በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ዋዜማ በጻፈው ፀረ አበሻ መጽሐፍ ገጽ 80 ላይ ያሰፈረውን ይመለከቷል።
"በእርግጥም አንድ ዓይነት ያበሻ ሕዝብ የለም፤ ያለው ግን አንድ እስከ 20% ከጠቅላላው ሕዝብ የሚሆን አነስተኛ ዐማራ በኢትጵያ ንጉሥ ነገሥት ግዛት ውስጥ የሚኖሩትን......" (Abyssinien Schwarze Gefahr, 1935, P.80)
ሁለተኛ ኦቦ ታመነ ቢተማና ጀርመናዊው ዩርገን ሽቶይበር እ.አአ 1983 ዓም ያልተፈታው የብሔር ጥያቄ በኢትዮጵያ (Die ungeloeste nationale Fragen in Aethiopien ) በሚል ርዕስ ገጽ 25 ላይ ጥቂት የኢትዮጵያ ጎሳዎችን የሚያሳይ ካርታ ነድፈው በዚያን ወቅት የነበረውን ጠቅላላ ሕዝብ ብዛት 33 ሚሊዎን አድርገው ከዚህም ውስጥ 50% ኦሮሞ፣ 20% አማራ፣ 10% ትግሬ፤ 5% ሱማሌ፣ 1.6 % አፋር እያሉ ፀረ አበሻ ድርሰት ጽፈዋል።

ወያኔ ኢሕአዴግ በምዕራባውያን በተለይ በአሜሪካና እንግሊዝ መንግሥታት አዲስ አበባ ላይ ከመሾሙ በፊት በዓለም የሚታወቀው የዐማራው ሕዝብ ብዛት 38% ሲሆን የኦሮሞው ደግሞ 35% ነበር። (Ecyclopeadia Britannica, 1991) በ1977 ዓም በተደረገው ትክክለኛ የሕዝብ ቆጠራ ውጤት 39 በመቶ ዐማራ ሲሆን 34 በመቶ ኦሮሞ (ጋላ) ነበር።
ወያኔ-ሻዕቢያ ትግሬን ለሥልጣን ኮርቻ ያበቁት የምዕራባውያን ስለላ ድርጅቶች እነ ሲአይኤ ያማራውን ሕዝብ ቁጥር አሳንሰው እንዲያውም ለአናሳው የትግሬ ጎሳ ማሟሊያ አደረጉት። ከትግሬ ጋራ 32% እያሉ በኢንተርኔት መገናኛ አናፍሰዋል። ያማራው ሕዝብ ብዛት ተቀናንሶ 20% ብቻ ነው ብለው ይዘላብዳሉ። የወያኔ ዘረኛ

ቅጥረኞች የሕዝብ ቆጠራ አደረግን ብለው የጌቶቻቸውን ግምት በድጋሜ አስተጋብቷል። ይህስ አያስገርመንም። ማንም ወደደ ጠላ ያማራው ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ ትልቁ ወገን ነው። ግን ለምን ዐማራውን ከጉራጌ፣ ከአርጎባ፣ ከሲዳማ፣ ከሃድያ፣ ከጋሞና የም ጋራ አልተቆጠረም?
ሃያ ከመቶ የተባለው ምትሃታዊ ቁጥር ሳይሆን ይቀራል! ከ60 ዓመት በላይ የማይለወጥ ውሱን ቁጥር ነው።
የ"ቤተሰብ መምሪያ ዕቅድ" በዐማራ ክልል ተብየው እንደ አሸን ፈልተዋል። ከድርጅቶቹ ተወካይ አንዷ ፈረንጅ ለቢቢሲ ዓለም አቀፍ ራዲዎ አገልግሎት በሰጠችው ቃለ ምልልስ ይህ አካባቢ ከመላው ኢትይጵያ በሕዝብ ሰፈራ ብዛት ከፍተኛ ነው በማለት ተናግራላች። ይህም ምትሃታዊውን ቁጥር 20 ይቃረናል።

በፕሮፓጋንዳው መስክ በኢትዮጵያ ያሉት ሱማሌ ጎሳዎችን ብቻ በተለይም የኡጋዴን አውራጃን አስመልክቶ በከፍተኛ ማጋነን አምስት ሚሊዎን አድርስውታል። ሐቁ ግን የሱማሌ ክልል ተብዬው እንደ ጉራጌ፣ ከምባታና ሃድያ፣ ትግሬ፣ ወሎ፣ ሸዋ፣ ወዘተረፈ ጥቅጥቅ ያለ የሕዝብ ሰፈራ የሌለበት፣ የተለያዩ ዘላን ጎሳዎች ተበታትነው የሚኖሩበት ነው። ጠቅላላው የሐረርጌ ክፍለ አገር ሕዝብ እንኳ አምስት ሚሊዎን አይሆንም። የጉራጌ ሕዝብ ቁጥር በመላው ኢትዮጵያ ከሱማሌው ጎሣ በጣም በልጦ ሳለ በፀረ ኢትዮጵያ ሴረኞች አነስተኛ እንደሆነ ተደርጓል። የአዲስ አበባን ነዋሪ ሕዝብና የዐማራ ክልል ተብየውን ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር እንደተለመደው አሳንሰው ወሻክተዋል። ከስባት ሚሊዩን በለይ የሚሆነውን አዲስ አበቤ በራሱ ነፃ ምርጭያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዳይተዳደር ወያኔ ትግሬና ተለጣፊ ጠባብ ጎሰኛ ወረሞዎች ዋና እንቅፋት ሆነውበት ቁም ስቅሉን ያያል።

## የኦነግ የፕሮፓጋንዳ ቀልቀሎ /ስልቻ/

ኦነግ ለ"ኦሮሚያ" መንግሥት እውን መሆን ተመኝቶ የሚጠቀምበት አዲስ ዘዴ የፈጠረውን የውሸት ታሪክ በተቀነባብረ መልክ ማስረጨት ነው። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ብቻ ነው። ዐማሮች የኦሮሞዎችን የገዳ ሪፑብሊክ በጉልበት መጥተው ይዘዋል፣ የገዳ "ዴሞክራሲያዊ" ሥርዓትን ዐማሮች አጥፍተዋል። ኢትዮጵያ በአውሮፓ ኤምፔሪያሊስቶች ርዳታና ፈቃድ የተመሠረተች አገር ናት።
ኦነግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ርስ በርስ ለማቃቃር የማይፈንቅለው ድንጋይ ከቶ የለም። ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ አብሶም ዐማራውና ወረሞው ለዘመናት አብሮ በመኖር ተዋልደው፣ ተጋብተው በደም ተሳስረው የሚኖሩ ናቸው። ስለሆነም የጋራ ፖለቲካዊና፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን በአንድነት ለማቃለል ተወያይቶ በጋራ መፍትሔ ለማግኘት በመጣር ፈንታ ግዜው በአልፈበት የጎሣ ፖለቲካ ስሜት በጥላቻ ዓይን ለመተያየት ማንኛውም የኢትዮጵያ ባላገር ሕዝብ ምኞትም ፍላጎትም የሌለው መሆኑ የተረጋገጠ ነው።
እነ ወያኔ-ሻዕቢያና ኦነግ በኢትዮጵያ አገርነት፤ በሕዝቧ መፈቃቀርና ወንድማማችነት ኪሳራ ለማትረፍ የተነሱ ቅጥረኛ ከፋፋዮችና ዘረኞች ናቸው። ኦነግ ተብዬው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት መጠናከር፣ ለማዕከላዊ መንግሥት መገንባት ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱትን የወረሞ (ጋላ) ተወላጅ ኢትዮጵያውያንን ለምሳሌ እንደ ራስ ጎበና አባ ዳጬ፣ ፊታውራሪ ኃብተ ጊወርጊስ ዲንገዴ (አባ መላ)፤ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ወዘተረፈ የመሳሰሉትን ሁሉ ዘወትር ይኮንናል። በፋሽስት ወረራ ወቅት ይሁን በሰሜንና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ለአገራቸው ከፋሽስት ርዝራዥ ባንዳ አስካሪ ውላጆች ገንጣይ አስገንጣይ በየጠሩ ግንባር ከሌሎች ወንድሞቻቸው ጋራ በፀረ አንድነቶች ጥይት የወደቁትን ክቡር የወረሞ አርበኞችን ታሪክና ማንነት ጥላሸት ለመቀባት ከፋፋዮችና ጎሰኞች ሁሉ ይቃዝናሉ። በወንድማማችነት፣ በፍቅርና በሰላም ተረዳድቶ የኖረውንና የሚኖረውን ሕዝብ በጎሳ ጥላቻ ስብከት ለማቃቃር ዘወትር ያዳክራሉ። ጭካኔ የተሞላበት አረመኔ ጭፍጨፋ አድርገው ኢትዮጵያውያንን በዘር በጎሳ አለያይተው፤ ለበዝባዥች አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር በመመኘት በደቡብ አፍሪቃ ተወግዞ የተወገደውን የባንቱስታን አፓርታይድ ሥርዓት በቀለሙ፣ በዘሩ፣ በደም ትስስሩ፣ በእምነቱና አንድ በሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጎሣ ፓለቲካ እንዲሰፍን በቅጥር ነፍሰ ገዳዩች ተፈርዶበታል። "ዲሞክራሲ"፣ የራስን በራስ ማስተዳደር እስከ መገንጠል፤ በራስ ቋንቋ በላቲን ቁቢ ፊደል መጠቀም" በሚባሉት ጨንበሎች የሚሸረበው ሴራ ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለውስጥና ለውጭ ጠላቶች መፈንጭያ ለማስደርግ እንጂ በእርግጥ ለሕዝቡስ ዘላቂ ጥቅምና እድገት ታስቦ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ፍትህ፣ እኩልነት፣ የሰብአዊ መብት መከበር፣ ዕድገትና ልማት በጎሳ በመለያየትናና በመገነጣጠል የሚመጡ ቢሆን ኖሮ ከማንኛው ሌላ አገር ይልቅ በቅድሚያ በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች (USA)፣ በካናዳ፣ በጣሊያን፣ በፈረንሳይ፣ በእስፓኝ፣ በእንግሊዝ ወዘተርፈ. ውስጥ በተግባር ላይ መዋል ነበረበት። በሴራ ፖለቲካ

የተገነጠለችው ኤርትራም ከዘጠኝ የጎሳ ክልል አልተሸነሸነችም። እንድ ቋንቋና ሃይማኖት ያላቸው የሱማሌ ልዩ ልዩ ጎሳ አባቆሮዎች ርስ ብርስ የሚጋደሉት፣ በምሥራቅ አውሮፓ ይጎዝላቢያ የተበታተነችው፣ በአፍሪቃ በላይቤሪያና በሩዋንዳ በብሩንዲ ያ ሁሉ ሕይወት ያለፈው በጎሳ ፖለቲካ ቅስቀሳ ነው። የዘረኞችና ከፋፋዮች የጎሳ ስሜት ስብከትና ቅስቀሳ ሥልጣን በአቋርጭ ለማግኘትና በቅጥረኛነት የባሕር ማዶ ጌቶቻቸውን ጥቅም ለማስከበር ብቻ እንጂ ለሕዝብስ ደንታ የለቸውም።

ሌላው ፍሬ ከርስኪ ከሆነው ፍጹም ተራ ስድብና አሉባልታ በመጽሑፍ መልክ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች ባማርኛ (ለምሳሌ ሞቲ ቢያ "ከውርስ ውሸቶች በስተጀርባ Stockolm, 1999 ) የቀረበውን ይገነዘቧል። በእንግሊዘኛና ጀርመንኛም ተዘጋጅቶ በስፋት ይሰራጭያል። ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ስለ "ኦሮሞ ታሪክ፣ ባሕል" ወዘተ. እየተባለ በፀረ-ኢትዮጵያ ወገኖች ከፍተኛ የገንዘብና ቁሳቁስ ርዳታ በየአለበት እየተዘጋጁ የቀረቡት "ጥናቶች" የሚባሉት አፈ-ታሪክና የለየለት ልብ ወለድ ፈጠራ "የኦሮሞ ምሁራን" በሚባሉት ግለሰቦች ስም ተጽፎ ይታተማል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ እ.አ.አ በ1993 ዓ.ም ለኦሮሚያ ነፃ ማውጭያ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዓለም አቀፍ ጉባኤ የተባለው (International conference on Ressource Mobilization for the liberation of Oromia) በኒዩርክ ተዘጋጅቶ እንደነበር ይታወሳል።

እንዲሁም ለኦሮሚያ ነፃነትና የፀረ-ኢትዮጵያ በተለይም ፀረ-ዐማራ ጥላቻ ዘመቻ አራጋቢው፤ ለዕልቂት ቀስቃሽ ቀንድኛ አስተባባሪና ሰባኪ ለሆነው እንግሊዛዊው ፖል ባክስተር ምስጋና መስጭያ ተብሎ አንድ ሌላ ጉባኤ ተዘጋጅቶ እዚያም "ምሁራን" የተባሉት ጋሎችና የባሕር ማዶ ጠባቂዎቻቸው ያቀረቧቸው ጽሑፎች ተደጉሰው " A River of Blessings" የምርቃት ወንዝ የተባለው የኢትዩጵያ መርገሚያ መጽሐፍ ተብዩ በአሜሪካ እ,አአ በ1994 ታትሟል። በተጨማሪም "የኦሮሚያ ነፃ" አውጭ ተባባሪ ፈረንጆችና ድርጎኞቻቸው ባንድነት በእንግሊዙ ፖል ባክስተርና በጣሊያናዊው አሌክሳንድሮ ትሩኡሊዝ ዋና ደራሲነት " Being and Becoming Oromo- Historical and anthropological enquires" ባማርኛ "ኦሮሞ መሆንና ለመሆን ታሪካዊና ሥነ ስብአዊ ምርምሮች" የተሰኘ በአብዛኛው ያው የተለመደውን ፀረ-ኢትዩጵያ የዘረኞች ልብ-ወለድና ፀረ-ጥቁር ሕዝብ ሐተታ የያዘ መጽሐፍ ኦፕስላ ስዊድን ኖርዲስክ ኢንስቲትዩት ታትሟል።

ከዚህም ሌላ ብቅ ጥልቅ የሚሉ ቋሚ መጽሔቶች መውጣታቸው አልቀረም። ለምሳሌም Oromo Studies, Oromo commentary etc የመሳሰሉት ይገኖበታል። እንዲሁም በስዊድን፤ በሆላንድ፤ በእንግሊዝ፣ በጀርመን፣ በአሜሪካ የሚዘጋጁት መጽሔቶች የኦሮሞ ነፃ አውጭዎችን ፕሮፓጋንዳ በሰፊው ያስተናግዳሉ።

ይህ ሁሉ የውሸት ፈጠራ የጋላ ታሪክ በምዕራባውያን የስለላ ድርጅት በተለይም በጀርመን፤ በስዊድን፣ በኖርዌ፣ በሆላንድና በእንግሊዝ የታቀደ የረጅም ዘመን ፀረ-ኢትዩጵያ የኢምፔርያሊስቶችና የነጭ ዘር የበላይነት ስሜት አራጋቢዎች ደባ ነው። በተለይ ወረሞዎችን በሚመለከት አሜሪካኖች ዋና ሃላፊነቱን ለጀርመን መንግሥት አስረክበዋል። ስለዚህም ነው የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኦፊሴል "ኦሮሚያ ሪፑብሊክ"ን ኢትዩጵያ ውስጥ ለማቋቋም የጀርመን የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን የሚያካሂዱትን ማናቸውም ድጋፍ ለማጠናከር ኦፊሴላዊ ፖሊሲ እንዳላቸው ተስተውሏል። ለምዕራባውያን በተለይም ለጀርመን፣ ለሆላንድ፣ ለኖሮዌ፣ ለእንግሎዝና ስዊድን መንግሥታት የሰብአዊ መብት በኢትዩጵያ መረገጥ፤ የሕሊና እስረኞች እስከ ሞት ድረስ በእስር መሰቃየት፤ መሞት በእስር ቤት ዕንበለ ፍትሕ መጋዝ፣ የጋዜጠኞች ያለ ሕግ መማቀቅ፣ መሰቃየት ሌላም የመብትና የነፃነት ረገጣ ሳይሆን የ "ኦሮሚያ ሪፑብሊክ" ኢትዩጵያ ውስጥ መመሥረት እንደሆነ ሳያመነቱ በግልጽ ይናገሩታል።

የኦነግ የውሸት ክምር ትላንት ሻዕቢያና መሰሎቹ የ "ኤርትራ ታሪክ" ብለው ለብዙ ዓመታት ሲያዘንቡት የነበረውና ያሉት የውሸት ጎርፍ የሚቀዱት ከአንድ ምንጭ ነው:: የዓለምን ሕዝብ በውሸት ፕሮፓጋንዳ ጠቅጥቀው በማሳመን "ውሸት ሲደጋገም ዕውነት ይሆናል" በሚል ዕምነት የትግላቸው መሣሪያ አድርገውት የፕሮፓጋንዳና የሥነ ልቦናዊ ጦርነት ከአርባ ዓመታት በላይ ሲያካሂዱ መቆየታቸው ይታወቃል።:

ኤርትራ የኢትየጵያ የሥልጣኔ መነሻ ምንጭ ከሆኑት ክፍለ ሀገራት አንዷ እንዳልሆነች ሁሉ ኤርትራ አረብ ነች፣ ከኢትዩጵያ ጋር ምንም ዓይነት የዘርም ሆነ የባሕልና የሃይማኖት ወይም የቋንቋ ግንኙነት የላትም፣ የኤርትራ ጉዳይ **ዐማራው የፈጠረው የቅኝ ግዛት ጉዳይ ነው** እየተባለ ለብዙ ዓመታት ሲያደነቁሩ መኖራቸው ከቶ መቼ ይዘነጋል።

ይህንን የመሰለውንን "የኤርትራ ታሪክ" ነው ሐቀኛው እንግሊዛዊው ምሁር ፓትሪክ ጅልክስ መቋጠሪያ የሌለው የፈጠራ ተውፌት "mythology" ብለው የጠሩት (Eritrea: Historiography and mythology; Affrican Affairs 1991 ገጽ 622) ::

ፓትሪክ ከኢጣሊያ ቅኝ ግዛት በፊት ማለትም ከ1885 ዓ.ም ኤርትራ የሚባል ሀገር እንዳልነበረና የዘጠኝ ጎሳዎች ሀገር የሆነችውን ኤርትራ (መረብ ምላሽ) በታሪኳ

ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ አንድ አካል እንደነበረች አስታውሰዋል።

በኢትዮጵያ ላይ የሚወርደውን የውሸት ውርጅብኝ በሚመለከት ረገድ የሚችጋን ዩኒቨርስቲ አሜሪካዊው የታሪክ ምሁር የተከበሩ ሃሮልድ ማርኪስ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ በማጣመምና በውሸት ዝባዝንኪ ከረጢት በመሙላት የሚካሄደውን ዘመቻና ውንጀላ በግልጽ አጋልጠዋል። ያለፈው ምን ሃላፊነት በኢትዮጵያ አለው? (<< Does the past have any authority in Ethiopia >>) በሚል ርዕስ ኢትዮጵያን ሪቪው መጽሔት 2(4) April 1992 እንዲሁም የኢትዮጵያን ታሪክ ማክሰር " The corruption of the Ethiopian history (1992) በተሰኘ ርዕስ በተለይም ስለ አዲሱ የኦሮሞ (ጋላ) ዘመናዊ ምሁር ዶክተር መሐመድ ሐሰን መጽሐፍ (The Oromo of Ethiopia...) የሰጡትን አስተያየት ማገናዘብ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

## <u>ነፍጠኛው ማነው?</u>

የኦነግ ፕሮፓጋንዳ ነቹ ምሁር ተብዬ ካድሬዎች እንዳሚሉት "የኢትዮጵያ ችግር የኢምፓየር ችግር ነው" እያሉ እንዳሚቀዣብሩት ሳይሆን ዕውነቱ ዛሬም እንደ ትናንቱ የጥቂት ወረሞ ሊሂቃን ችግር ሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የደቡብ፣ የምዕራብና ምሥራቅ ነባሩን ሕዝቡን ጨፍልቆና ጨፍጭፎ፣ አቃጥሎና አባሮ ቀሪውን ባሪያ (ገባሮ) ለማድረግ ያደረባቸው አባዜ ነው።

የጋሞ ተወላጅ የተከበሩ አቶ አሰፋ ጨቦ <u>ነፍጠኛው ማነው</u> በሚል ርዕስ ለጦቢያ መጽሔት ቅፅ 6 ቁጥር 8 1991 ባቀረቡት ጽሑፍ ስለ ጋላ ወረራ ስያነሱ ያገራችውን ተወላጅ አባ ባሕርይን በመጥቀስ፤

"ኦሮሞ ዛሬ ባሊ፣ አርሲ፣ ሐረርጌ፣ ጅማ፣ ወለጋ፣ ሸዋ፣ ኢሉባቦር የምንላቸውን አካባቢዎች ያዘ። ዛሬ የሲዳማና ግዲኦ አውራጃዎች በኦሮሞ መሓል ደሴት ሆነው የሚታዩት በወቅቱ ወረራውን ተቋቁመው ያመለጡ ናቸው።..... እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ ነጥብ አለ። ኦሮሞ ወሮ የያዘው ባዶ መሬት አልነበረም። ብዙ በአካባቢው የነበሩት የደረጁ የበጁ ያካባቢ መንግሥታትን አጥፍቶ ነው። በሚሊዮን የሚቆጠሩ አባ ባሕርዩችን ሕይወትና ንብረት አውድሞ ነው።..........."

በመቀጠልም አሰፋ ጨቦ ነፍጠኛው ማነው? ለሚለው ጥያቄ ሲመልሱ፤ በገሙ ጎፋ ጋርዱላ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው፣ በደርግ የመሬት አዋጅ ሳቢያ የአካባቢው ሕዝብ በነፍጠኞች ላይ ተነስቶ እንደነበር አስታውሰው፤ " የጋርዱላ አውራጃ ነፍጠኛ በሙሉ ኦሮሞ መሰለኝ፣ ያያታቸውን ስም ስመለከት በሙሉ ኦሮሞ አያት ነበራቸው። በሃይማኖት ትንሽ ተለያይታችሁ እንደሆነ እንጅ የተነሳባችሁ ኦሮሞ ነው ብዬ አስማምቼ ተመልስኩ። እነሱ ግን ዐማራ ነን ብለው አምነዋል፣ የወዳቻ (ገሙገፋ) ነፍጠኛ ኦሮሞ ዐማራ ነኝ ይላል። ኦሮሞ ነኝ የሚልም አይመስለኝም። የጨንቻ ሰው ሌላ የዋጠው ባህል ስለ ሌለ የጨንቻ ኦሮሞ ሁሉ ነፍጠኛ ባህል አንዳለው ነው የማውቀው። ትምባሆ (ሱርት) ይቅማሉ። ፈጭያሳ ያደርጋሉ። ቃልቻም ያለ መሰለኝ። ሰው ለመቅበር ካልሆነ በስተቀር ቤተ ክርስቲያን አላየኋችቸውም። ...ይህ እላይ የተገለጠው የጋሞ ጎፋ ሞዴል በአብዛኛው ለሲዳሞ፣ ለአሩሲ፣ ለባሊ፣ ለሐረርጌ ወዘተረፈ የሚውል ይመስለኛል። በተለይም ለሲዳሞ አብዛኛው የጋሞ ኦሮሞ ነፍጠኛ ይርጋለም ዲላ አለታ ወንዶ ሀገረ ማርያም ወንድም አኅት ክስት እንዳላቸውና ጠይቀውም እንደሚመጡ አውቃለሁ።..."

አቶ አሰፋ ስለ ኦነግ "ኦሮሚያ" የተረት ልበ ወለድ (mythical) ሪፑብሊክ ካርታ አንስተው፤

"ከአዲስ አበባ ደቡብ ምሥራቅና ምዕራብ ባሉት የኢትዮጵያ ገዛቶች ከኦሮሞ በስተቀር ሌላ ብሔረሰብ ነገድ ጎሣ የለበትም። በኔ አስተያየት ከላይ የተጠቀሰው ሁሉ ከታሪካዊው እውነት ውጭ ነው። ምንጩ የፖለቲካ ብልጠት ወይም ድንቁርና ይመስለኛል። ....ማስተዋልም ይጎድለዋል። "የጋራ ቤታችን" የሚል ማስተዋል ስለሚጎድላቸው" የጋራ ቤታችንን" ለማፍርስ ታጥቀው ይሠራሉ። የጋራ ቤታችን የሚፈልገውን መጠነኛ ጥገና በማካሄድ ፋንታ ከመሠረቱ መናዱን የመረጡ ይመስላሉ።"

## <u>የደቡብ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት የዘረኞችና የጎሰኞች ጠር</u>

በአጠቃላይ ሲነገር የደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕዝብ በመጋቢት 1984 ዓ.ም "የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክርሲያዊ ሕብረት" የተባለውን ድርጅት አቋቁመው የወያኔ ሻዕቢያን የጎሣ ክልል ዘረኛ ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲና የፈጠራ ኢታሪካዊ የሆነውን የባንቱስታን ክልል አንቀበልም፣ አንከፋፈልም ብለው በሕብረት ለመተዳደር ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ወያኔ ሻዕቢያ ከ25 ሚሊውን በላይ የሚሆነውን ኢትዮጵያዊ ሕዝብ በሚወክሉት ነገዶች (ጉራጌ፣ ሃድያ፣ ከምባታ፣ የም፣ ከፋ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ጊዲኦ፣ ቡርጂ፣ ጋሞ፣

ዐማሮ፣ ኩሉ ኮንታ፣ ወዘተ.) ላይ ለማዳከም ታስቦ አንዳንድ ሆዳሞችን በገንዘብና ሹመት እየደለለ ተለጣፊ አሸንጓሊት ድርጅቶችን በመፍጠር ቅጥረኞችና ምልምሎችን በማስታጠቅ የደቡብን ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ቁም ስቅሉን ያሳዩታል። ሰቆቃው የበዛበት ወገንም ሀገሩን እየለቀቀ እንዲሰደድ መደረጉን የወላይታና የጊዲኦ አካባቢዎች ቋሚ ምስክር ናቸው። ወያኔ ትግሬ የፋሽስት ጣሊያን ዘረኛ ፖለቲካን አስፈጻሚ ሆነ ነፃ ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ በማስጥፋት የምዕራባውያን አሸንጓሊቶች የኤርትራና የትግሬ ሪፑብሊክ የቅርጭፆ ክፍያ ለማድረግ አሰበው እንደ ፋሽስቱ የጣሊያን ወረራ ዘመን ለኢትዮጵያ ሕልውና፣ ልዕልና አንድነትና ነፃነት የቆመውን ግለሰብም ሆነ ሕዝባዊ ድርጅት ሁሉ የኢምፔሪያሊዝምና የቅጥረኞቹ የግፍ ጽዋ ተቀባይ እንዲሆን የተፈረደበት ወቅት ነው።

ጀግናው የደቡብ ሕዝብ በአንድነት ጸንቶ ለኢትዮጵያዊነቱ እንዲታገሉ ያደረጋው አንዱም ዐቢይ ምክንያት በጋላ ወረራ ዘመናት በአካባቢው የደረሰውን የሕይወትን ውድመት ሳያበቃ አሁን ደግሞ በመካከላቸው ከእነሱ በሉባ ወረሪ ተቀምቶ በተወሰደው ሰፊ ለም አገር ላይ ታሪክ የማያውቀውን የፈጠራ "ኦሮሚያ ክልል" የሚባል ግዛት አካግ ለመፍጠር ያቀደውን አሸንጓሊት መደንቀር በታሪክ ያዩትንና የኖሩትን የጋላ ሉባ ወራሪዎች ዘግናኝ ትውስታ ዛሬም በድጋሚ ሥራ ላይ ይውል ይሆን በሚል ግንዛቦት ነው።

ይህ በጋሞ ብቻ ሳይሆን በጥንታዊው ሃድያ፣ በሲዳማ፣ በየም፣ በከፋ፣ በአፋር፣ በኢሣ፣ እስከ ሱዳን ጠረፍ ሁሉ ተስፋፍቶ የሚታይ የኢትዮጵያኖች ስጋት ነው።
ይህን በተመለከተ የሃደያው ተወላጅ አቶ ሃይሌ አርፊቾ ሲጽፉ የ"ኦሮሚያ" ጉዳይ በደቡብ ኢትዮጵያ ሰላም እንዳይሰፍን የሚያደርግ ሁኔታ እየፈጠረ መሆኑን ደጋግመው አብራርተዋል። በአጠቃላይም ወያኔ በ1983 አዲስ አበባ ዘምቶ በብቸኛዋ ልዕለ ኃያል አሜሪካና እንግሊዝ መልካም ፈቃድና ትብብር በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተፈናጠጠ ጀምሮ በደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የዘር፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የወሰን ግጭቶች እንዳላቋረጡና በዚህም ሳቢያ የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕይወት እንዳለፈ፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ንብረት እንደወደመ ገልጽዋል። በተለይ ያሩሲ አርባ ጉጉን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በመጥቀስ ከዐማርኛ ተናጋሪው ሌላ የሃድያ፣ የከምባታ፣ የወላይታና የጉራጌ ተወላጆች በግፍ እንደተገደሉ አስታውሰዋል። የተከበሩ አቶ ሃይሌ አርፊቾ (ነፍሳቸው ትማር) ከዚህም ጋር በማያያዝ ሲያስረዱ፣

"የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሕዝቦች በረጅም ታሪካቸው፣ በሰላም በጦርነት በንግድ በጋብቻ አንዱ ከሌላው እየወሰድ ያዳበሩት ኢትዮጵያዊ እሚያሰኝ የባሕል፣ የሥነ ልቡናና የቋንቋ መለያ አፍርተዋል። በሌላ በኩል ሲታይም ደግሞ የዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ የቋንቋ ክፍፍል፣ በዘር ላይ የተመሠረተ አይደለም። ለምሳሌ የዛሬዎች የአርሲ ኦሮምኛ (ጋሊኛ) ተናጋሪዎች ብዙዎቹ የሃድያ ተወላጆችን የሚያጠቃልሉ ናቸው። እንደ ዕውነቱ ከሆነ በአርሲ እስከ ሁለት ሚሊዮን ይደርሳሉ ተብሎ የሚገመተው የሃድያ ተወላጆች በቁጥር ከኦሮሞ የሚወለዱትን ይበልጣል። የዛሬ 370 ዓመት ከተፈጸመው የወረሞ ወይም ጋላ ወረራ በፊት የሃድያ ግዛት ሰፊ የሆነ ከስምጥ ሸለቆ ሐይቆች (ዟይ፣ አዋሳ፣ ላንጋኖ፤ ሻላ፣ አቢያታ፣ ጨው ባሕር) በግራና በቀኝ የሚገኙ፣ ሸዋ፣ ባሊና ሲዳሞን የሚያዋስን ነበረ። " ብለዋል።
ይህንንም ለማረጋገጥ የዘር የቋንቋ የሃይማኖትና የባሕል ጥናት ባለሙያ ጀርመናዊው ተመራማሪ ኡልሪህ ብራውካምፕር ስለ 17ኛና 18ኛው ክፍለ ዘመን የሃድያ ግዛት ያቀረቡትን ጽሑፍ ጠቅሰዋል። (Die Geschichte der Hadya in Süd-Aethiopien) እኝህ ተመራማሪ እንደጻፉት፤

"ከአዋሽ እስከ ገናሌ ወንዝ፣ ከዟይ እስከ ዋቢ ሸበሌ ባለው በዛሬው አሩሲና አካባቢው ሁለት ዓይነት ባሕል ጎን ለጎን ሲያድጉ ቆይተዋል። በአንድ በኩል በቁጥር አነስተኛ የሆኑት የጋላ ገዳ ሥርዓት ና ሃይማኖት ተከታዮች፣ በሌላ በኩል ሁለት ሦስተኛ የሚሆነው በቁጥር ከፍተኛ የሆነው የሃድያ ሕዝብ በአብዛኛው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነበሩ። "

ይህ የዛሬውን የወያኔና የ "ኦሮሚያ ነፃ" አውጭዎችን የዘር ፕሮፓጋንዳና ክልል የሚቃረን በመሆኑ ወያኔና አካግን የሚያስቆጣ ቢሆንም አሌ የማይባል ሐቅ ነው ሲሉ አቶ ሃይሌ አርፊቾ ተናግረዋል። በመቀጠልም ይህም ሁኔታ ሃድያን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የብዙ የደቡብ ምሥራቅና ደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ብሔሮችን የታሪክ ሂደት የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል። በመሆኑም ዛሬ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች የራሳቸው ያልሆነ ከውጭ በግዳጅ የተቀበሉትን ቋንቋ ስለሚናገሩ፣ ወያኔ ዘርና ቋንቋን አንድ አድርጎ "ክልል" እያሉ ኢትዮጵያን በልበ-ወለድ ጎሣዎች ሸንሻኖ እንደ ፋሽስት ጣሊያን የሚያስተዳድሩበትን ዘይቤ በአጽንኦት ተቃውመዋል። የግዳጅ ጎሣና ቋንቋ ፖለቲካ ውጤት ደግሞ እንደምናየው የማይቋርጥ ግጭትና ደም መፋሰስ ነው በማለት አረጋግጠዋል።
ራቅ ብለን ደግሞ ወደ ምዕራብ ደቡብ ኢትዮጵያ ጠረፍ ስንሄድ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ዜጎች የጋላን ነፍጠኝነት በተመለከተ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ከ18ኛው እስከ

19ው ክፍለ ዘመን በተካሄደው የሚጭያ ጋላ ጎሣ ወራሪዎች ነባሩን ሕዝብ ፈጅተው፣ አባረው ሀገሩን አቃጥለው ምድረ በዳ ካደረጉት በኃላ ተመቻችተው ሰፍረዋል። በሕይወት የተረፈውን ሕዝብ ገበሮ ባሪያ አድርገው ቋንቋውን ጭምር አስለውጦታል። የታወቁት የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች (ቢዛሞ፣ ጋፉት፣ ጋምቦ፣ ዳሞት፣ ጅንጃሮ (የም)፣ እናሪያ፣ ዜት፣ ሻት፣ ጎንጋ፣ ጎማር፣ ቦሻ፣ ወዘተ.) ከነስማቸው ተሰርዘው ሀገራቸው በሙሉ ወይም በአብዛው በዘላኑ ጋላ ተነጥቀው ዛሬ ኢሉባቦር፣ ወለጋ፣ ጅማ የሚሉት የጋላ ነገድ ስም ተሰጧቸዋል።

ለከብቱ ልም ግጦሽ መሬት ፍለጋ የመጣው ዘላን ልዩ ልዩ ጎሳ በሉባ የወረራ ስልት ባገኘው ለም ስፍራ ቋሚ ቤት ሠርቶ፣ የርሻ ሥራን ከነባሩ ሕዝብ ተምሮ ከአዲስ የላቀ የሥልጣኔ ደረጃ ደረሰ። ይህም ሥር ነቀል ለውጥ የወራሪውን ጋላ ልዩልዩ ነገዶች የዘር፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖትና ባጠቃላይም የባህል ሁኔታ ቀይሮታል። የገደ የዘለን የወል ሥርዓት አክትሞ እንደ ሰፈረበት አካባቢ ሁኔታ የጋላ ንጉሣዊ ሥርዓትና መሳፍንት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በ18ኛው ክፍለ ዘመን የጅማ፤ የሊሙ እናሪያ፣ የጌራ፣ ወዘተረፈ ተመስርተው የባሪያ ንግድ ሲያደርጉ መቆየታቸው የተረጋገጠ ነው።

በኢትዮጵያ የግዛት ወሰን ውስጥ ያለው የትኛውም አገር፣ አውራጃ፣ ወረዳና ቀበሌ፣ የትኛውም ስፍራ የመላው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ አንጡራ ሃብት እንጂ ለወረሞ፣ ለዐማራ፣ ለትግሬ፣ ለጉራጌ፣ ለሃድያ፣ ለሲዳማ፣ ለሱማሌ ወዘተ ነገድ <u>ብቻ ተለይቶ የሚከለል በጭራሽ</u> ያለመሆኑን ይወቁ። የባንቱስታን የጎሣ ክልል እንደ ደቡብ አፍሪቃ ተወግዶ ይቀበራል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃና ዲሞክራሲያዊ ውሳኔና ይሁንታ ክፍለ ሀገራዊ ያካባቢ አስተዳደር ይመሠርታል።

በኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራዊ የራስ ገዝ ሥርዓት ከአክሱም ነገስታት በፊት ጀምሮ ያለ የነበረ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት መንግሥት ልዩ ታሪክና ባሕል ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈረንጅ ርጥባን **የጎሣ ፌደራሊዝም** የድንጋይ ዘመን የጎሣ ፖለቲካ ሥርዓትን አሽቀንጥሮ ይጥላዋል።

ስለዚህ እንደ ወያኔ-ሻዕቢያና ኦነግ ወዘተ የመሳሰሉት ቅጥረኞች ፀረ-ኢትዮጵያ ተልዕኮ የዓለም ዘረኞች ሴራና ተንኮል ስለሆነ የጥቁር ዘር ሁሉ አውቆት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ማሳወቅ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ዜጋ ሁሉ ግዴታና ተግባር ነው። ዘረኞች የኢትዮጵያን ጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ፣ ባሕልና ሃይማኖት ለማጥላላት በሳይንስና ታሪክ ሽፋን ሐቁን አጣመውና ዘቅዝቀው በውሸት መጋረጃ ሸፋፍነው አነብንበዋል፣ ያነበንባሉም።

ለምሳሌ ያህል እንኳን ብንጠቅስ አሽከርና ገረድ፣ ሎሌ፣ ባለሚል፤ የቀን ሙያተኛ ወዘተ. የመሳሰሉትን የማኅበረሰብ ግኑኝነቶች እንዲያው በጅምላ "ባሪያ" እንደሆኑ አስመስለው ጽፈዋል፣ ተርከዋል፣ ይተርካሉም።

የንጉሥ አሽከሮች፤ ባለሚሎች፣ ሥራ ቤቶች ወዘተ. በፈረንጅ እይታ ባሪያዎች ናቸው። ዳሩ ግን ባገራችን አሽከር ወይም ሎሌ እንዲሁም ገረድ በደሞዝ የሚተዳደሩ መሆናቸውን እንበለ እፍረት ሸፍጠው እንደራሳቸው የባሪያ ቃል ትርጉምና ድርጊት አድርገው አትተዋል። በጥንታዊት ኢትዮጵያ አንድ ሎሌ ወይም ገረድ በዓመት ደሞዝ ይቀጠራል። ደሞዙንም በዓይነት (እህል) ወይም በገንዘብ (አሞሌ) ይከፈለዋል።

ኢትዮጵያ አገራችን እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ምጣኔ ሃብቷ የፈረንጅ ከበርቴዎች ጥገኛ አልነበረም። ባለገሩ ሕዝብ ለኑሮው የሚያስፈልገውን ሁሉ እራሱ እያመረተ ለውጭ ንግድ አቅርቦትም መጠነኛ ችሎታ ነበረው። ይህን ሁኔታ ለመቀይርና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በቀጥታ ለመቆጣጠር ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የእንግሊዝ፣ የጣሊያንና የፈረንሳይ ቅኝገዥዎች ከፍተኛ ምኞትና ሴራ ሲያውጠነጥኑ ነበር። ቢቻል በዲፕሎማሲ ካልሆነም በጦር ወረራ ኢትዮጵያን ለመያዝ ያልፈነቀሉት ድንጋይ ከቶ አልነበረም። የዛሬው ያገራችን ሁኔታ ሲያያዝ የመጣ እንጂ የድንገት ክስተት ፈጽሞ አይደለም።

የአውሮፓ ክርስቲያን ነንባዩች ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ጥቁር አፍሪቃውያንን ዘርፈውና አድነው ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ማዶ በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ ባሮችን እንደ በርበሬና ጨው ሲቸረችሩ የነበሩት "ሥልጡን" ነጮች በኢትዮጵያ የባሪያ ንግድ ይካሄዳል እያሉ በዚህ ሰበብና ሽፋን ፀረ-ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ ነዝተዋል። ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ማኅበር አባል እንዳትሆን የእንግሊዝ ዘረኞች ያደርጉ የነበረውን ሴራ የሱዛን ማየርና የማርቲን ክላይን ጥናት (Slavery and colonial rule in Africa , (1999) pp 17-35) ይመለከቷል። የኢትዮጵያን ብቸኛ ነፃ ጥቁር መንግሥት በዓለም ላይ ለማጥላላት ታስቦ ኢትዮጵያ ዋና የባሪያ ነጋዴ እንደሆነች ፈልስመው አራግበዋል። በአንጻሩ ደግሞ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች በናይጀሪያ፤ በሴራሊዎን፣ በሱዳን በጆርዳን ወዘተረፈ ባሪያ ንግድ እስከ 20ኛ ክፍለ ዘመን ድረስ ቆይቷል።

የኢትዮጵያ አጢ መንግሥት በጦር ምርኮ ከሚወስዳቸውና ክርስቲያን አድርጎ ከሚያኖራቸው በስተቀር ባሮችን እየፈነገለ ለውጭ ገበያ በጭራሽ አቅርቦ አያውቅም።

# የኢትዮጵያውያን ጥቁር አይደሉም ሽፍጥ

"ኢትዮጵያውያን ጥቁር አፍሪቃውያን አይደለንም ይላሉ" እየተባለ የምዕራብ ዘረኞች ፀረ ኢትዮጵያ ቅጥፈትን ቅጥረኛው ኦነግ ሰምቶ ያራግባል:: የጋላው ምሁር መሓመድ ሐሰን ኢትዮጵያውያን የራሳቸው ቋንቋ፤ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ ያላቸው መሆኑ እሱንና ጌቶቹን ከፍተኛ ቅናትና ምቀኝት አሳድሮባቸው በጥቁር ሕዝብ ጥላቻ ያጠናቀሩትን ሲያቀነቅን ቀጥሎ ያለውን ጽፏል፤

" .. They( Abyssinians) played down their Africaness. Christian and Negro were ofetn cited as opposite, as good and evile. Oromos or Galla as it was called, derived from Africa..." ( The Oromo of Ethiopia; A History 1570- 1860, Cambridge: 1990, P 3)

በአድዋ ጦርነት ድባቅ የተመቱ፣ ከኛ በላይ ሰው የለም ባይ የጥቁርን ዘርያ በመካነ እንስሳት አጉረው ትዕይንት ሲያሳዩ በነበረበት ወቅት፤ በአፍሪቃ ጥቁር ሕዝብ በኢትዮጵያ ጀግኖች እጅ የደረሰባቸውን ከፍተኛ ቅሌትና ክስረት ለመሸፋፈን፤ በተለይም በዓለም ዙሪያ ነፃነቱን ለመቀዳጀት፣ ዘረኝነትንና ቅኝግዛትን ለማውደም ቆርጦ የተነሳውን ጭቁን ሕዝብ ሁሉ አጋርና ተባባሪ፣ አርአያና ምሳሌ ለማሳጣት የምዕራብ አውሮፓ ዘረኞች ተመኝተው የፈጣራ ወሬ አቀናበረዋል:: ከአድዋ ድል መልስ ኢትዮጵያውያን ጥቁር አፍሪቃውያን ሆነን እንዳልሆንንና ከአረቢያ የሳባ አሠልጣኝ ሠፋሪዎች ዝርያ ወገን መደበውን የጥቁር ሕዝቦችን ሕብረትና አንድነት ለያይቶ ለመግዛት ከተሸረበው ስልት አንዱ የሆነውን የጋላ ቅጥረኞች ሲያነበንቡት ማየትና መስማት ዝቃጭነታቸውን ያሳያል:: የ"ኦሮሞ" ነገድ አፈቀላጤ ነኝ ባይ ጆን ሶርንሶን ይህንኑ ስልት ሲያናፍስ " የአበሻ ምሁራን አፍሪቃዊ ማንነትን ክደው ከጥንት ዕብራውያን ጋራ በሰሎሞንና ንግሥተ ሳባ በኩል ላላቸው ግንኙነት ትኩረት ይሰጣሉ:: የአበሻ የጽሑፍ ታሪክ ኦሮሞዎችን ያገለለል ነው" በማለት ቀባጥሯል:: (Crisis and Terror in Horn of Afrcia,USA P 41)

ያይጥ ምስክሯ ድንቢጥ እንዲሉ ይህን ሃሳብ የኦነጉ አቢዩ ገለታ የወታደራዊ የደርግ ባለሥልጣን የነበረው የኦነግ የውጭ መምሪያ ሃላፊ ፀረ ኢትዮጵያ ጥላቻ ቅስቀሳ የኢትዮጵያ መጨቆኛ ሥርዓትና ውጤቱ (Ethiopian System of domination and consquences) በሚል ርእስ የአምላካዊ መብት የመጨቆኛ ምሳሌ ከሶርሰንና ብጤዎቹ ፀረ ሴማውያን የተነገረውን እንደ በቀቀን ሰምቶ ያስተጋባውን እንጠቅሳለን::

<< ... Menelik had to seek acceptance by European powers as a partner during the era of Africa. To claim legitimacy based on antiquity and divine authority of biblical proportion, the Abyssinians gave their empire the name " Ethiopia". There also emerged a racist belief that " they have a much higher form of intellegence than the purly Negro peoples of Africa." (htt://www.oromia.com/Articles/ Ethiopian_system_of_domination_and_ consequences)

ትርጉሙ፣

ምኒልክ ከአውሮፓ ኃይሎች ጋራ በአፍሪቃ ቅርጭያ ዘመን እንደ ተባባሪ እውቅና ለማግኘት መፈለግ ነበረበት:: በጥንታዊነትና በመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ሥልጣን አለኝ ማለት አበሾች ለግዛታቸው ኢትዮጵያ የሚል ስም ሰጥተዋል:: እነሱ ከንጹሕ የአፍሪቃ ጥቋቁሮች እጅግ በጣም የላቀ ብልኅነት አላቸው የሚል የዘረኝነት እምነት ተፈጥሯል:: >>

ይህ ዓይነቱ የቅናት ወሬ የተቀናበረው በችኮ መንቻካ የነጭ ዘር የበላይነት አናፋሾች መሆኑ ግልጽ ነው:: ውሻ በበላበት ይጮኻል እንዲሉ የኦነግ ድርጎኞች ለእንደዚህ ያለ ተራ ቅጥረኝት ዓይናቸውን በጨው አጥበው፣ በኢትዮጵያዊነት ላይ ፍጹም ጭፍን ጥላቻ ተክነው፣ አበሻ ባለመሆናቸው እጅግ በጣም በቁጭት በሽታ ሕሊናቸውን የሳቱና የኢትዮጳያን ሕዝብና መንግሥት የረጅም ዘመናት ታሪክና ሥልጣኔ የዐማራው ብቻ እንደሆነ ተደርጎ የተነገራቸውና፣ የሚመስላቸው ወገኖች ሁሉ በፀረ ሴማውያን ያውሮፓ ዘረኞች የከሰረ ርዕዩት የተመለመሉና የተካኑ ናቸው:: ላውሮፓ ዘረኞች የኢትዮጵያ መንግሥት በአባይ ሸለቆና ቀይ ባሕር ዳርቻ መኖር የረመጥ እሳት፣ ያይናቸው ውስጥ ጉድፍ ሆኖባቸው ቆይቷል:: በመሆኑም ሕዝቡን በጎሳና በሃይማኖት ከፋፍሎ በማቃረን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ከአልተቻለም ለማዳከም የሚቻለው ኢትዮጵያዊነት ወድሞ ጣባብ ጎሰኝነት ሲሰፍን ብቻ እንደሆነ ተግንዝበዋል:: ስለሆነም ላንዱ ቋንቋ ተናጋሪ ጠበቃና ሞግዚት፣ አዛኝ ቅቤ አንጓች ሆነው ይቀርባሉ:: ታማኝ ቅጥረኛ መስሎ ለታያቸው ውዳሴ ከንቱ ይደረድሩለታል:: የገዛ ወገኑን፣ ወንድሙን እንዲጠላ ይቀሰቅሱታል:: ቅኝገዥዎች ኢትዮጵያን ለመያዝ የጎሰኝነት እሳት በማቀጣጠል ብቻ ይሳካልናል ብለው ጎምዥተዋል:: ጠባብ ጎሰኖችም ሥልጣን በአቋራጭ ይዘው ለመበዝበዝና ለማስበዝበዝ ይቋምጣሉ::

ከተጨባጩ ሁኔታ አንጻር ጋሎች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ በኢትዮጵያ ምድር ከሠፈሩበት ጊዜ ጀምሮ የተደረገው መስተጋብር ተጽፏል:: ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ ዜጋ ሳይሆኑ አበሾች ለምን ስለ ነገደ ጋላ አልጻፉም ከተባለ ተገቢው ጥያቄ ለምን ሁሉን ነገር አዋቂና ሥልጡን ነኝ ባዩች ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስለ "ኦሮሞ" ለምን ጽፈው

አላቆዩም? አውሮፓ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በጭለማ ኑሮ ይዳክር ስለነበር እንኳንስ ስለ ነገደ ጋላ ታሪክ ሊጽፉ ይቅርና ከምዕራብ አውሮፓ ሌላ ምድር መኖሩን እንኳ ፍጹም የማያውቅ፣ መሠልጠንም የጀመረው በሴማውያን ይሁዲ ሰፋሪዎችና ከእስላም አረብ ሥልጣኔ በመቅዳት ነው።

የመካከለኛው ምሥራቅ ጥንት ነዋሪዎች ዕብራውያን፣ ሱማሪያን፣ አረቦች ወዘተረፈ ሁሉም የነጭ ሕዝብ ዘርያ አይደሉም። የጠይም ቀይና ጥቁር ዘርያ ነበሩ እንጂ። በዓለም ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በአፍሪቃዊነቱ፣ በጥቁርነቱ፣ በነፃነት ወዳድነቱ ከመኩራቱ በስተቀር ከቶ ምንም ግዜ ከነጭ የፈረንጅ ወገን ነኝ ብሎም አይውቅም። በተለይ የሰሜን አሜሪካ የአውሮፓ ሰፋሪ ቅኝገዥ ወራሪዎች የአንግሎ ሳክሶን የነጭ ዘር ላዕላይነት ስሜት አራጋቢዎች ኢትዮጵያውያን ኔግሮ አይደለንም ይላሉ ብለው ከአፍሪቃ በባርነት ቀንበር ሰርቀው ላሻገሩዋቸው ጥቁር አሜሪካውያን በሰፊው የወሻክቱላቸው እንደነበር ታዋቂው የነፃነት ታጋይ ማልኮልም ኤክስ አፍሪቃን ሲገበኝ አዲስ አበባ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ የተገነዘበውን እዚህ ላይ መጥቀሱ ሁኔታውን ግልጽ ያደርገዋል።

" So, I went through khartoum to Addis Ababa, Ethiopia, which is a wonderful country. It has its problems, and it's still a wonderful country.
Some of the most beautiful people I've seen are in Ethiopia, and most intellegent and most dignified, right there in Ethiopia. You hear all kinds of propaganda about Ethiopia. But any time a person tries to tell you as they've told you and me, that Ethiopians don't think they're the same as we are, that's some of that man's manufacturing. He made that up ...They are just as friendly towards us as anybody else is." (G. Breitman; *By any means Necessary*, (London: 1985), p. 142)

ትርጉሙ፣

ከካርቱም ወደ አዲስ አበባ ውብ ድንቅ ከሆነችው አገር ኢትዮጵያ ተጓዝኩ። የራሷ ችግሮች ቢኖራትም እንኳ ውብ ድንቅ አገር ናት። ካየኋቸው እጅግ በጣም ቆንጆ ሰዎች በኢትዮጵያ ያሉት ናቸው፣ በጣም ብልሆችና የተከበሩትንም በዚያው በኢትዮጵያ ነው የሚገኙት። ስለ ኢትዮጵያ ሁሉንም ዓይነት ፕሮፓጋንዳ ትሰማላችሁ። ሰውዬው ዘወትር ሊነግራችሁ እንደሚሞክረው፣ ለኔ ለናንተም እንድነገሩን ኢትዮጵያውያን እንደኛ እንደሆኑ አያስቡም፣ ይህስ ያ ሰው ከፈጠረው ጥቂቱ ብቻ ነው። ውሸቱ ነው።.. እንደማንኛውም ሌላው ሕዝብ ሁሉ እነሱ ለኛ ወዳጆቻችን ናቸው።

በምድረ አሜሪካ ፀር ጥቁር ዘረኝነት ድርጅታዊ ቅርፅ ነበረው፣ ዛሬም እንኳን አለው። ጥቁር አሜሪካውያን የፀረ ዘረኝነት ታጋዮች የአሜሪካንን ድርጅታዊ ዘረኝነት ሲያገናዝቡ "ኔግሮ" ለሚሉት ቃል ዘረኛ ነጮች የሰጡት ትርጓሜ ታሪክ፣ ሥልጣኔ፣ ባሕል፣ ሃይማኖት የሌለው፣ በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ፣ በእንግሊዙ ቻርለስ ዳርዊን የፈጠራ ዝግም ለውጥ ሂደት እሳቦት ገና የመለወጥ ክውነትን ያልጨረሱት፣ ምንጪያቸው ከጨለማው አህጉር አፍሪቃ በለው ከሚጠሩት፤ በምዕራብ አውሮፓ ክልስልስ የባሪያ ፈንጋይ ውላጆች ማለት በፖርቱጋሎች፣ በእስፓኞች፤ በእንግሊዞች፣ በሆላንዶችና ሌሎች ከአፍሪቃ ለተሠረቁት ጥቁር ሕዝቦች መጠሪያነት የተሰየመ ሰለሆነከቶ በምንም ዓይነት ተቀባይነት እንደሌለው በማመልከታቸው ነው ዛሬ "ኔግሮ" የተባለው ቃል ውድቅ ተደርጎ ጥቁር አሜሪካዊ ወይም አፍሪቃ አሜሪካዊ (African American) እየተባሉ መጠራት የተጀመረው።
ታዲያ! ኢትዮጵያውያን በአፍሪቃ አባይ ሸለቆ ጥንትም፣ ዛሬም ለወደፊቱም ጥቁር አፍሪቃውያን ነበርን፣ ነን እንጂ ያውሮፓ ዘረኛ ስያሜ የንቀትና የጥቁር ጥላቻ መጠሪያ ቃል "ኔግሮ" ከሁሉ አስቀድመን አለመቀበላችን በዓለም ጥቁር ሕዝብ ዘርያዎች ዘንድ ያኮራናል። በቅኝ ተገዥነት ቀንበር ስር ለወደቁት ሁሉ መመኪያ የነፃነት ጮራ ፈንጣቂ ኮከብ አስደርጎናል። በመሆኑም ዘረኞችና ምንደኞቻቸው ፀረ ኢትይጵያ የፈጠራ ወሬ ቢያናፍሱ ፈጽሞ አያስገርምም። ታላቁ አርብኛ የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ሐኪም ዶክተር መላኩ በያን የአሜሪካና ካሬቢክ የጥቁር ሕዝብ ዘርያ ወንድሞቻችንን ሁሉ በማስተባበር ፀረ ዘረኝነት፣ ፀረ ፋሽሽት ትግሉን ከታላቋ እንግሊዛዊት ወይዘሮ ሲልቪያ ፓንክረስት ጋራ በመተባበር አከናወኗል። ዶክተር መላኩ በያን ነው ከሁሉ አስቀድሞ "ኔግሮ" የተሰኘ የነጭ ዘር የበላይነት ስሜት አራጋቢዎች ያወጡትን መጠሪያ ቃል በመቃወም ጥቁር አሜሪካዊ ተብለው እንዲጠሩ ያሳወቀው።

በፋሽሽት ጣሊያን አረመኔያዊ ወረራ ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም ጥቁር አሜሪካወያን ከኢትዮጵያወያን ወንድሞቻቸው ጎን በመቆም ይልቁንም በአእሜሪካ ታላላቅ ከተሞች ለምሳሌ በኒዮርክ ሀርለም፤ በፔንሲልቫኒያ ወዘተረፈ. ያደረጉት ጸረ ፋሽሽት የተቃወሞ ሰልፍ ዘወትር ይታወሳል። የጣሊያን ዘርያ ያላቸው አሜሪካዊ ተብዬ ድቅልቅል ውላጆች ደግሞ በወራዳው አረመኔ በዱቼ ሙሶሎኒ ማኅራትና በፈጠረው <የጥቁር ሸሚዝ> ነፍሰ ገዳይ ምልምል ካድሬዎቹ የአበሻን ጥቁር ሕዝብ ፍጹም አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በመደገፍ የጣሊያን ዘርያ ተብዬ ስደተኛ ሰፋሪዎች ፈንጠዝያ ሲያደርጉ ጥቁር አሜሪካወያን ሱቆቻቸወንና የንግድ ድርጅቶቻቸወን መሰባበራቸው ተመዝግቧል (Peter Alexander et al. 2000, PP. 18-23)።

የጋላ ነፃ አውጪው ኦነግ እና የሻዕቢያ ምልምል ትሕነግ የፀረ ኢትዮጵያ የጥቁር ሕዝብ ጠላቶች ቅጥረኞችና ምልምል ጋጋኖዎች ናቸው። ስለሆነም በፀረ ኢትዮጵያ የጥቁር ሕዝብ ጠላቶች የተጋቱትንና በሉ የተባሉትን ሰምተው ፀረ ዐማራ ጥላቻ ሲነዙና ሲስተጋቡ ቆይተዋል፣ ያስተጋባሉም።

የምዕራብ አውሮፓ ዘረኞች የጥንት ግብፅ ጥቁር ሕዝብን ታሪክና ሥልጣኔ ከአፍሪቃ አህጉር ለይተው የአውሮፓና እሲያ ነጭ ሠፋሪዎች ፈጠራ እንድሆነ አስመስለው እንደዋሹት ሁሉ የኢትዮጵያንም ጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ ታሪክ፣ ባሕል፣ ፊደል፣ ሥነ ጽሑፍ በጠቅላላወ ከአፍሪቃ ወጭ ከአወሮጳና ከእሲያ የመጡ "ነጮች ፈጠራ ነወ" እያሉ የቀዣበሩት እንቶፈንቶ በሳይንሳዊ ጥናት ውድቅ ተደርጓል።

# ክፍል ፫ ይቀጥላል.................................................................

# ሰለ ቁቢ የላቲን ፊደል ፖለቲካዊ ውሳኔ

እነ ፕሮፌሰር አዩ ሞሚና
ድክተር ገብሬ ጉልቱ፤
ድክተር የውብዳር ዘለቀ
ዶክተር ገለበው ሰንገጎ
ገሞራው ማንያዘዋል
አስተያየትና ግንዛቤ ለማቅረብ ቢፈልጉ፣

tomy.gemora16@gmail.com